


# ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፍያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን (SAMP) - NEPA የአካባቢ ግምገማ

## በበለጠ ለማውቅ

### 1. ዘላቂ የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን ምንድን ነው?

ቀጣይነት ያለው የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን (SAMP) በሲያትል-ታኮማ ኣለም ዓቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ (SEA) የወደፊቱን የተተነበየ ፍላጎት ለማሟላት የለውጥ ንድፍ ነው። የአውሮፕላን ማረፊያ መሠረተ ንድፍ/ፕላን እ.ኤ.አ. በ 2018 ተጠናቅቋል ። በአለምአቀፍ የአየር መጓጓዣ ማህበር እንደተገለጸው ፣ 56 ሚሊዮን አመታዊ መንገደኞችን እንዲሁም የበረራ እና የጭነት እንቅስቃሴን ለማገልገል የታቀዱ 31 የቅርብ ጊዜ ንድፎች/ፕሮጀክቶች (NTPs) ተለይቷል (IATA)።

SAMP NTPs በ FAA ሁኔታዊ ይሁንታ አግኝተዋል እና የ NTPs የአካባቢ ግምገማ የማካተት ሂደት ተጠናቅቋል። በአሁኑ ወቅት የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ (NEPA) የአካባቢ ጥበቃ ግምገማ በመካሄድ ላይ ሲሆን ረቂቅ NEPA ሰነድ በ 2024 ይለቀቃል ተብሎ ይጠበቃል. የ NEPA ሂደቱ እንደተጠናቀቀ፣ የግዛቱ የአካባቢው ጥበቃ ህገ ደንብፖሊሲ (SEPA) ግምገማ ይከተላል።

### 2. የቀረበው ንድፍ/ፕሮጀክት ሃሳብ ምንድ ነው?

የNTPs ዋና ዋና ቁልፍ ሃሳቦች(ማለትም፣ የግብይት ተግባር) ከእነዚህም መካከል ጎላ ያሉ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው:- ሁለተኛ ተርሚናል/መውጫ ግንባታ፣ ማዕከላዊ ጥገና ምድረ ግቢ፣ ከአውሮፕላን ማረፊያ ውጪ ያሉ የጭነት ማጓጓዣ ቦታዎች፣ የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶች እንደገና እንዲገጣጠሙ ማድረግና የነዳጅ ማምረቻ ዎች መስፋፋት ይገኙበታል።

- ሁለተኛ ተርሚናል/መውጫ 19 ተጨማሪ በሮች
- የአውቶቡስ መንገድ እና ጣቢያዎች
- አሁን ያለውን የኪራይ መኪና ተቋም፣ አዲስ ተርሚናል/መውጫ እና ዋና ተርሚናልን የሚያገናኝ ከፍ ያለ የአውቶቡስ መንገድ እና ጣቢያዎች
- የአሁኑን መገልገያዎች ለመተካት እና የአየር ማጓጓዣን ለማስተናገድ የጭነት መገልገያዎች
- የአውሮፕላን ማረፊያ መንገዶችን ማደስ
- የአየር ማረፊያ ማሻሻያዎች የደህንነት እና ውጤታማነት ለማሻሻል
- ሁለተኛውን ተርሚናል ለማገልገል አዲስ የመኪና ማቆሚያ መሠረተ ልማት
- ለዘላቂ የአውሮፕላን ነዳጅ ተጨማሪ ተቋማት

### 3. የሲያትል ታኮማ ኣለም ኣቀፍ አየር ማረፊያ ማስፋፋት ለምን አስፈለገ?

በ2021 በፒዩጅት ሳውንድ አካባቢ ምክር ቤት የተካሄደ አንድ የአካባቢ ያየር ማመላለሻ ጥናት እንዳሳየው፣ በተተነበየው ፍላጎት መሰረት በየዓመቱ 27 ሚሊዮን የሚሳፈሩ መንገደኞች እንዳሉ እና በ2050 ሲይትል የተሻለ የአገልግሎት ደረጃ በተመቻቸ ደረጃ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ይሆናል።

ለወደፊት ለታቀደው ፍላጎት አዲስ መገልገያዎች ከሌሉ በሲይትል የኣይሮፕላን ማረፍይ ዙርይ መጨናነቅ ይጨምራል ፣ ይህም ተጨማሪ መዘግየቶችን እና የከፋ የአገልግሎት ደረጃን ያስከትላል።



# አካባቢያዊ ግምገማ

## 1. ምን አማራጮች እየተመለከቱ ናቸው?

አማራጮቹ የታቀደው እርምጃ፣ የተቀላቀለ ተርሚናል አማራጭ እና እርምጃ የለሽ አማራጭን ያካትታሉ። ሁለቱም የታቀደው እርምጃ እና የድብልቅ ተርሚናል አማራጭ ማሻሻያዎችን ያካትታሉ፣ የ ተቀላቀለ የተሻለ የአገልግሎት ደረጃ አማራጭ አዲስ ተርሚናል/መውጫ እና በሮች እንዲገነቡ ሀሳብ አቅርቧል። የ ምንም እርምጃ ኣይስፈልግም አማራጭ ምንም ተጨማሪ የፌደራል እርምጃዎች ወይም አካላዊ ማሻሻያዎችን አይገምትም።

## 2. የታቀዱት ድርጊቶች ሊከሰቱ የሚችሉ የአካባቢ ተፅእኖዎች ምን ምን ናቸው?

የአካባቢ ምዘና (EA) በአየር ጥራት፣ ጫጫታ እና የገጽታ መጓጓዣ ላይ ተጽእኖዎችን ለይቷል። ነገር ግን፣ በትክክለኛ የመቀነስ እርምጃዎች፣ እነዚህ ተፅዕኖዎች ከጉልህ ደረጃ በታች እንደሚቆዩ ይጠበቃል።

## 3. ፕሮጀክቱ/ውጥን በአካባቢው መጓጓዣ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

የፕሮጀክቱ/ውጥን ተፅእኖ በአካባቢው ወለል መጓጓዣ ላይ ተንትኗል። አንዳንድ መስቀለኛ መንገዶች መጨናነቅ ሊያጋጥማቸው ቢችልም፣ ወደቡ የትራፊክ ፍሰትን ለማሻሻል እንደ የትራፊክ ምልክቶች መጨመር፣ መንገዶችን ማስፋት እና አደባባዮችን መገንባት የመቀነስ ስልቶችን አቅርቧል።

## 4. የአካባቢውን ተጽእኖዎችን ለመቀነስ ምን ዓይነት የቅናሽ እርምጃዎች ይተገበራሉ?

የመቀነስ እርምጃዎች የብክለት መከላከል ዕቅዶችን፣ የዝናብ ውሃ አስተዳደር ሥርዓቶችን፣ የእርጥበት መሬት መልሶ ማቋቋም እና አደገኛ የቁሳቁስ አወጋገድ እቅዶችን ያካትታሉ። እነዚህ እርምጃዎች በግንባታው ወቅት እና በኋላ ላይ ከፍተኛ የአካባቢ ተፅእኖዎችን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ያለመ ነው።



# የአካባቢ ግምገማ

## 1. የአካባቢ ግምገማ ዓላማ ምንድን ነው?

የአካባቢ ግምገማ ዓላማ የታቀደው ፕሮጀክት/ውጥን ከመከናወኑ በፊት ሊያመጣ የሚችለውን የአካባቢ ተጽዕኖ ለመገምገም ነው። ዋና ዓላማዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሙሉ ግልጽነት እና የህዝብ ተሳትፎ
- ህጎችን እና መመሪያዎችን ማክበር
- ተጽዕኖዎችን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለመቀነስ መንገዶችን መለየት

## 2. በ NEPA እና SEPA መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የብሔራዊ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ህግ፣ ወይም NEPA፣ የፌደራል መሪ ክርጅት/ኤጀንሲዎች ውሳኔ ከማድረጋቸው በፊት ያቀረቧቸውን ተግባራቶች የአካባቢ ተፅእኖን እንዲገመግሙ እና ለህዝብ ግብአት እድሎችን እንዲሰጡ የሚፈልግ የፌዴራል ፖሊሲ ነው። የፌዴራል አቪዬሽን አስተዳደር የ NEPA መሪ ድርጅት/ኤጀንሲ ነው።

የግዛቱ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ህግ ወይም SEPA በግዛቱ ደረጃ ያሉ ኤጀንሲዎች ተመሳሳይ ነገር እንዲያደርጉ ይጠይቃል። NEPA EAን ተከትሎ፣ ወደቡ በሴፓ ስር የተለየ የአካባቢ ግምገማ ያካሂዳል።

የሲያትል ወደብ በስቴት ህግ የ SEPA መሪ ድርጅት/ኤጀንሲ ነው።

## 3. የአካባቢ ግምገማ (EA) ምንድን ነው?

የፌደራል እርምጃ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል ወይ የሚለውን ለመወሰን የአካባቢ ግምገማ (EA) ተዘጋጅቷል። የትኛውም እርምጃ በከፊል ያልተካተተ እና የአካባቢ ተጽዕኖ መግለጫ (EIS) የማይፈልግ፣ እርግጠኛ ያልሆኑ ተፅዕኖዎች ያለው፣ ወይም ያልተፈቱ የአካባቢ ጉዳዮች ያለው፣ የ EA ዝግጅት ያስፈልገዋል።

## 4. በEA ንድፍ ላይ እንዴት አስተያየት መስጠት እችላለሁ?

የ EA ንድፍ ላይ አስተያየት መስጠት ህዝብ በአካባቢያዊ የምርመራ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ እና ለውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አስተዋፅኦ ለማድረግ ወሳኝ መንገድ ነው። ወደቡ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል የሕዝብ አስተያየት ለመስጠት የሚቻልበትን መንገድ ለማዘጋጀት ቃል ገብቶኣል።

የህብረተሰቡ አባላት በስድስት ቋንቋዎች የተተረጎሙ መረጃዎችን መገምገም እና በአስተያየቱ ጊዜ ውስጥ አስተያየቶችን በህዝባዊ ስብሰባ ፣ በመስመር ላይ ፣ በኢሜል ወይም በመደበኛ ፖስታ ውስጥ ማስገባት ይችላሉ። ሰነዱ በSAMP ድህረ ገጽ፣ በኤስኤኤ ኤርፖርት ኮንፈረንስ ማእከል እና በቡይሪይን፣ ዲሞይንስ፣ ፌደራል ዌል፣ ደቡብ ሲይትል፣ ሲታክ እና ተኩዊላ ውስጥ ባሉ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል። አስተያየቶች ኤጀንሲው የአስተያየት ሰጪውን አቋም እና የተነሱት ጉዳዮች ለምን ለውሳኔ አሰጣጡ ጠቃሚ እንደሆኑ እንዲረዳ በቂ ዝርዝር ማቅረብ አለባቸው።

የህዝባዊ ስብሰባዎች ውስጥ በአንዱ ላይ የህዝብ አስተያየትዎን ይስጡ፡-

- ማክሰኞ ኑቨምበር 12
  ዋይል ውድ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ፌዴራል ዌይ) ፣ ከምሽቱ 6 እስከ 8 ሰዓት
- ረቡዕ ኑቨምበር 13
  ማውንት ሪንየር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዴስ ሞይንስ) ከምሽቱ 6 እስከ 8 ሰዓት
- ሐሙስ ኑቨምበር 14
  ሃይላይን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቡይሪን)፣ ከምሽቱ 6 እስከ 8 ሰዓት
- ቅዳሜ ኑቨምበር 16
  የማክሚኬን ሃይትስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ሲታክ)፣ ከጠዋቱ 10 እስከ ከሰዓት 12 ሰዓት



በድረ-ገፃችን በኩል በመመዝገብ በመስመር ላይ ወይም በኢሜል በመላክ የህዝብ አስተያየት ያስገቡ፡-
ኢሜል፡ samp@portseattle.org
ድህረገፅ፡ https://www.sampntpenvironmentalreview.org/

የህዝብ አስተያየት በፖስታ አስገባ፡-

ደብዳቤ፡ ሚስተር ስቲቭ ራይቦልት
የሲያትል ወደብ
የአካባቢው ያየር ማመላለሻ እና ዘላቂነት
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 68727
ሲያትል፣ ዋሽንግቶን 98168

የድምፅ፣ የምስል፣ ወይም የቋንቋ እርዳታ የሚያስፈልግ ከሆነ እባክዎ በ 206-339-0213 መልዕክት ይተዉ።

## 5. የሕዝብ አስተያየት ጊዜ ምን ያህል ይሆናል?

ወደብ ለ NEPA EA መደበኛውን የ30 ቀን የህዝብ አስተያየት ጊዜ እንዲራዘም በመጠየቁ ምክንያት FAA የ45-ቀን አስተያየት ጊዜ አረጋግጧል። በበዓል ሰሞን፣ ውስብስብነቱ እና የትንታኔው ርዝማኔ፣ እና የጥቁር፣ የአገሬው ተወላጆች፣ የቀለም ህዝቦች (BIPOC) እና ሌሎች በታሪክ ውክልና የሌላቸው ማህበረሰቦች መዳረሻን በማረጋገጥ ወደቡ እንዲራዘምለት ጠይቋል።

አዲስ መረጃ፡ በኤፍኤኤ ውስጥ ያሉ የፌዴራል ባልደረባዎቻችን የኤጀንሲውን እና የህዝብ አስተያየት ጊዜን ለአስተያየቶች ወደ 53 ቀናት አራዝመዋል። የአስተያየቱ ጊዜ ዓርብ፣ ዲሴምበር 13፣ 2024 ይዘጋል።

## 6. ከአስተያየቱ ጊዜ በኋላ ምን ይከናወናል?

በአስተያየቱ ጊዜ ማጠቃለያ ላይ ሁሉም የተቀበሉት አስተያየቶች በኤፍኤኤ እና ወደብ የመጨረሻውን EA በሚዘጋጅበት ጊዜ ይገመገማሉ እና ግምት ውስጥ ይገባሉ. ለአስተያየቶች የሚሰጡ ምላሾች በመጨረሻው EA ውስጥ ይካተታሉ።

## 7. በዚህ የበአካባቢያዊ ግምገማ ሂደት ኣካሔድ ውስጥ ማህበረሰቦችን በእንዴት ሁኔታ እያሳተፋችሁ ነው?

የህዝብ ተሳትፎ ጥረት በሁሉም የአካባቢ ግምገማ ሂደት ደረጃዎች በመስመር ላይ፣ በአካል እና በምናባዊ ተሳትፎ ከዋና ዋና የፕሮጀክት ክንውኖች ጋር የተጣጣመ ነው። ወደቡ ተደራሽ፣ ለመረዳት ለሚቻል የህዝብ አስተያየት ሂደት ቁርጠኛ ነው። አንድ ጊዜ የሕዝብ አስተያየት ጊዜ በጥቅምት 21፣ 2024 ከተከፈተ፣ የህብረተሰቡ አባላት በስድስት ቋንቋዎች የተተረጎሙ መረጃዎችን መከለስ እና በአስተያየቱ ጊዜ ውስጥ አስተያየቶችን በህዝባዊ ስብሰባ፣ በመስመር ላይ፣ በኢሜል ወይም በመደበኛ ፖስታ ማቅረብ ይችላሉ። ሰነዱ በድረ-ገጻችን እና በቢይሪይን፣ ዲሞይንስ፣ ፌደራልይ ዌይ፣ ሲታክ እና ሌሎችም ባሉ የህዝብ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል።

## 8. እንዴት ተጨማሪ ማወቅ እና በ SAMP አካባቢያዊ ግምገማ ኣካሄድ ሂደት ላይ ማሻሻያ ማድረግ እችላለሁ?

የበለጠ ለማወቅ የንድፉ/ፕሮጀክታችንን ድረ-ገጽ በwww.sampntpenvironmentalreview.org ይጎብኙ።



ኖቬምበር 11፣ 2024 ተዘምኗል